# ይህን ያውቁ ኖሯል ?

## ስለ ክርስቶስ ከክርስትና እምነት ውጭ የተሰጡ ምስክርነቶች

ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ ምድራዊ ሕይወትና ስለ ትምህርቱ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፈው ሁሉ እውነት መሆኑን በማረጋገጥ ፤ የባሕርይ አምላክና የዓለም መድኃኒት መሆኑን ያምናሉ ። ተአምራቱን ያደንቃሉ ። ይህ እንግዲህ በክርስትና እምነት ክልል ውስጥ የሚገኙ ተከታዮቹ የሚሰጡት ምስክርነት ነው ። ከክርስትና እምነት ውጭ ያሉት ክፍሎችስ ስለ ክርስቶስና ስለ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት እንዴት ነው ? በየዘመናቱ የተነሱ አያሌ ስመ ጥር ታሪክ ጸሐፊዎች ፤ የፍልስፍና ሊቃውንትና የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች ምንም እንኳ የባሕርይ አምላክ መሆኑን ባያምኑም ፤ ስለ ሰው ልጆች በጐ አኗኗር ፤ ስለ እኩልነት ፤ ስለ ፍትሕ ፤ ስለ እውነት የገለጠው ትምህርት በሌሎቹ የሃይማኖት መጻሕፍት ከተገለጠው ሁሉ የላቀ መሆኑን አረጋግጠው መስክረዋል ። ይህ ብቻ አይደለም ። በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፈው የማይገኙ ስለ ክርስቶስ የሚያወሱ ውብና አስደናቂ ታሪኮች ከእኒህ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ከማያምኑ ወገኖች ተጽፈው እስከ ዘመናችን ደርሰዋል ።

ጲላጦስ ምድረ ይሁዳን ይገዛ በነበረበት ዘመን (በ26-36 ዓ.ም. ) በሀገሪቱ ውስጥ የደረሰውን የፀጥታ መታጣት ሁኔታ አስመልክቶ በጻፈበት በዜና አይሁድ መጽሐፍ በ18ኛው ክፍል ዮሲፍ ወልደ ኮርዮን የሚከተለውን ጽፏል ። "በዚህ ጊዜ ውስጥ በእጁ ድንቅ-ድንቅ ሥራዎች የተደረጉ አንድ ታላቅ ሰው ተነስቶ ነበር እሱ ያደረጋቸውን ዓይነት ድንቅ ሥራዎች ( ተአምራት) ያደረገ ሰውን በእውነቱ እንዲያው እንዳልባሌ እንደተራ ሰው መጥቀሱ ትክክል መስሎ ስለማይታይ ይከብደኛል ። እንዲህ ከማለቱ ይልቅ እንዲያው ባጭሩ ሕዝበ እስራኤል የሚጠብቁት መሲሕ ማለቱ ይቀል መሰለኝ" ይላል ዮሴፍ ወልደ ካርዩን ፤ "ይህ ሰው በትምህርቱና በተአምራቱ ከሕዝብም ከአሕዛብም ( ከአይሁድና ከግሪክ ) ወገን ብዙዎቹን እንዲያምኑት እንዲከተሉት ያደረገ ነው ። በካህናት አለቆቻችንና በሽማግሌዎቻችን አነሳሽነት ጲላጦስ በመስቀል እንዲሞት በፈረደበት ጊዜ ፤ እኒህ በትምህርቱ አምነው በፍቅሩ ተስበው የተከተሉት ሰዎች እስከ መጨረሻው አልተውትም ። በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሥቶ ተገልጦ ታይቷቸዋልና ። ስለእነዚህ ማለት ሕማሙ ፤ ሞቱ ትንሣኤውና ስለ ሌሎች በሺህ ስለሚቆጠሩት ድንቅ ድንቅ ሥራዎቹ በቅዱሳን ነቢያት አስቀድሞ በተነገረለት መሠረት ፤ ክርስቲያኖች ተብለው በስሙ የተጠሩት እኒህ ወገኖቹ (ተከታዮቹ) እስከ ዛሬ አሉ"

ደግሞም የቤተ መቅደሱንና የቅጽሩን አሠራር ባወሳበት "የአይሁድ ጦርነቶች » በተሰኘው መጽሐፉ በአባቶቻቸው ዘመን የቤተ መቅደሱ መጋረጃ አንዲት ክር እንኳ ያልተመዘዘለት የሚያምር መጋረጃ እንደነበርና ክርስቶስን በመስቀል ላይ በሰቀሉበት ሰዓት ይህ መጋረጃ ከላይ እስከታች መቀደዱን ፤ ሌሎችም ፍርሃትና ጭንቀት ያመጡ ምልክቶች ( ተአምራት) መደረጋቸውን ልክ በወንጌል እንደተጻፈው አድርጎ ገልጦአል ።

ይህ ስለሰው ልጆች ደህንነት በጎ አሳቢ የሆነ ሰው ከተገደለና ከተቀበረ በኋላ ከሞት መነሣቱን ያረጋገጡ አሉ ሌሎች ደግሞ ወዳጆቹ /ተከታዮቹ/ በድኑን ሰርቀው ወስደውት እንጂ ፤ ከሞት አልተነሳም ያሉም አሉ ። እውነት የትኛው መሆኑን ግን ወስኜ መናገሩ አይሆንልኝም ፤ የሞተ ሰው በገዛ ኃይሉ ከሞት ሊነሳ እንደማይችል አውቃለሁና ። ግን



ትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 50 ኅዳር 1974

www.ethiopianorthodox.org

አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ለመነሣት ይችላል ከተባለ ፡ ያ ሰው አንድም በአንድ ጻድቅ ሰው ጸሎት የተነሳ መሆን አለበት ፡ አንድም መልአክ ወይም አርያማዊ (ሰማያዊ) መሆን አለበት ። አለበለዚያ ራሱ አምላክ የሰው ልጆችን ለመታደግ በአካለ ሥጋ ተገልጦ በሰዎች መካከል ኖሮ በገዛ ፈቃዱ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ ካልተነሣ በቀር ማንም ሰው ከሞተና ከተቀበረ በኋላ ሊነሳ አይችልም ከዚህም በላይ መቃብሩን ይጠብቀ የነበሩት 30 የሮማ ወታደሮችና የብዙ ብዙ ጭፍሮች ስለነበሩ ደቀመዛሙርቱ ሠረቀት ለማለት ፈጽሞ አይቻልም » ብሏል ።

ከዚህ በላይ የተመለከተውን ጽሑፍ ያነበበ ማናቸውም ሰው ጸሐፊው ዮሴፍ ወልደ ኰርዮን ክርስቲያን ሊመስለው ይችል ይሆናል ። እሱ ግን ኦሪታዊ - ከዚያውም ዘንድ ለሕጋቸውና ለሃይማኖታቸው ቀናዕያን ከሆኑት ከፈሪሳውያን ወገን ነበር ። በ2ኛው ምእት ዓመት የነበረው አርጌንስ ፡ በ4ኛውና በ5ኛው ምዕት ዓመት የነበሩት አውሳብዮስና ሶዞሜን ቃሉ የኦሪታዊው የዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ምስክርነት መሆኑን አረጋግጠው በየታሪክ መጽሐፋቸው መዝግበውታል ።

ስለ አንድ ታሪክ ወይም ድርጊት ራሱ ባለጉዳዩ ወይም የገዛ ወገኖቹ ከሚሰጡት ምስክርነት ይልቅ ፡ ከጉዳዩ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ሦስተኛ ወገኖች የሚሰጡት ምስክርነት የነገሩን ትክክለኛነት በበለጠ እንደሚያረጋግጥ የታወቀ ነው ። ስለዚህ ይህ ከክርስትና እምነት ውጭ የሆነ ፈሪሳዊ ስለ ክርስቶስ የሰጠው ምስክርነት ፡ እርሱን ከአድልዎ ነፃ የሆነ ታሪክ ጸሐፊ ሲያደርገው ፡ ስለ ክርስትና ሃይማኖት ምንነት እውነቱን ለመረዳት ለሚፈልጉ ወገኖችም ፡ እንደነዚህ ባሉት የክርስትናን እምነት ባልተቀበሉ ሰዎች የሚሰጡ ምስክርነቶች ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እንደ ተጨማሪ ማስረጃ ሆነው ሊያገለግሉ እንደሚችሉ አይጠረጠርም ።

እጅጉ ረታ

www.ethiopianorthodox.org